# በኮ/ል ደመቀ ስም ገንዘብ የሰበሰቡ እነ ጎንደር ሕብረትና ስዊድን አስሎ ሎንደን ሌሎች አካላት ገንዘቡን የት አደረሱት? የሚለው አጠያያቂ ነው። አሳዛኝም!

April 4, 2018

ይህ ኮ/ል ደመቀ ዘውዱ ይኖርበት የነበረው ቤት ነው። ሐምሌ 5/2008 ዓም በኮ/ል ደመቀ ላይ በተደረገ ጥቃት ኮ/ል ደመቀ እና ቤተሰቡ በሕዝብ ትግል ቢተርፉም ቤቱ ግን ፈራርሷል። በተለይ የመንግስት ኃይል ነኝ የሚሉት ፈንጅም ስለወረወሩበት ውስጡ ፈርሷል። በአሁኑ ወቅት ቤቱ ማንም አይኖርበትም።

በኮ/ል ደመቀ ላይ ጥቃት የፈፀሙት ትህነግ ያዘዛቸው ታጣቂዎች ናቸው። የአማራ ክልል መንግስት እንኳ አያውቃቸውም። በዚህ ጥቃት ቤቱ ፈርሷል። ያፈረሰው የመንግስት ጥቃት ነው። በዚህ ወቅት ቤታቸው ጉዳት ደርሶበታል የተባሉ ሰዎች ከመንግስት ካዝና በርካታ ሚሊዮን ብር ሲከፈላቸው የዚህ ቤት ባለቤትን ዞር ብሎ ያየው የለም። ለሕዝብ ትግል መሰረት የሆነን ቤት አጥቶ ማንም አልጠየቀውም። ሌላው ይቅር ከሀምሌ 2008 ዓም ጀምሮ ያለውን ኪራይ እንኳ የሚታገስ አይገኝም! የዚህ ቤት ባለቤት ግን ምንም አላለም። ዝም ተባለ፣ እሱም ዝም አለ! እሱ ኩሩ ነው፣ የእሱ ኩሩነት ግን ያገባኛል የሚለውን ማሸማቀቅ፣ ማሳፈር ነበረበት! በተግባር የሚያፍር ጠፋ!

የመንግስቱ የመንግስት ነው። የታወቀ ነው! በዚህ ጥቃት ምክንያት የተፈጠረውን እምብይተኝነት ብዙ ሰው ሲኮራበት ይስተዋላል። ከዚህ ያለፈ ነገር ግን ያለ አይመስልም። የቤቱ ባለቤት አሁንም ድረስ መሸጥም የፈለገ አይመስልም። በእርግጥ የመንግስት አካላት ይህን ቤት እንደሚፈልጉት እየተገለፀ ነው። አላማው ደግሞ በኮ/ል ደመቀ ላይ ብቻ ሳይሆን በሕዝብ ላይ የተፈፀመውን ጥቃት ትውስቱ እንዳይኖር ለማድረግ ነው!

በዚህ አጋጣሚ ለትግሉ እቀርባለሁ የሚለውንም አካል ሚና መጥቀስ ተገቢ ነው። የኮ/ል ደመቀ ፎቶ በዶላር እንደተሸጠ የሚታወቅ ነው። ጎንደር ሕብረት በኮ/ል ስም በተለያዩ ስብሰባዎች ገንዘብ መሰብሰቡም እርግጥ ነው። ሌሎች አካላትም ሰብስበው ይሆናል። እነዚህ በእስረኛ ስም የሰበሰቡ አካላት ገንዘቡን የት አደረሱት? የሚለው ግን አጠያያቂ ነው። አሳዛኝም!

በኮ/ል ደመቀ ስም ገንዘብ አሰባስቧል የተባለው የጎንደር ሕብረት ገንዘቡን ለኮ/ል ስለማድረሱ ለቤተሰቡ ቅርብ የሆነን ሰው ስጠይቅ ያገኘሁት መልስ አስደንጋጭ ነበር። ጉዳዩ ይበልጥ ግልፅ ይሆን ዘንድ ቤተሰቦቹን ጠይቄ ያገኘሁት መልስም ተመሳሳይ ነው። ከአንድ ወገን ብቻ መጠየቁ አግባብ ስላልሆነ ከህብረቱ ቅርበት አለን የሚሉ ሁለት ሰዎችን ስጠይቅ "ልከናል" ብለው ከመድረቅ ውጭ አሳማኝ መልስ ማግኘት አልቻልኩም። ከምንም በላይ ተገኝቼ ያየሁትን ማመን ነበረብኝ፣ የቤተሰቡ ሁኔታ ያሳምናል! የቤቱ ሁኔታ ያሳምናል!

ከመንግስት በተጨማሪ በሕዝብ ስም ገንዘብ እየሰበሰቡ ያሉትን መጠየቅ ያለብን ይመስለኛል። ጉዳዩ የእስረኛ ስለሆነ፣ እኔም የቻልኩትን ጠይቄያለሁ። ፎቶ የገዛ፣ ስብሰባ ላይ ገንዘቡን ያወጣ፣ በወር፣ በአመት መዋጮ የከፈለ ሁሉ "ሰጥተናል ያላችሁትን በማስረጃ አቅርቡ" ብሎ መጠየቅ አለበት። እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ካልጠሩ ትግሉ ሲንከባለል መኖሩ ነው!

በተለይ ስቶክሆልም ስዊድን ፣ ኖርዊየ አስሎ ፣ ሎንደን ፣